



# አበበች ጎበና ሄዬ

በጎ አድራጊ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት መሪ



## “ከቦርሳዬ ውስጥ ዳቦ አውጥቼ ለሁለት ልጆች ልሰጣቸው ስሞክር፣ ፖሊሶች ደርሰው ‘ከዚህ አካባቢ ጥፊ’ አሉኝ። ‘እሞታታለሁ እንጂ ንቅንቅ አልልም’ አልኳቸው።”

የ ህይወቴን አቅጣጫ የቀየረው ወሎ ውስጥ የሚገኘውን የግሸን ማርያም ገዳም ለመሳለም ስሄድ ያጋጠመኝ ሰቆቃ ነበር። እድሜዬ አርባ አጋማሽ ላይ ነበር፤ ብዙ ሺህ ሰዎች በረሃብ ሲሰቃዩ ተመልክቼ ዓለም ተገለባበጠብኝ። ሁለት ወላጆቻቸውን በሞት የተነጠቁ ህፃናትን ለማሳደግ ወደ አዲስ አበባ ይዤ ተመለስኩ። ወዲያው የረሃብ ተጎጂዎች ወደ አዲስ አበባ መጉረፍ ስለጀመሩ እኔም በየጎዳናው የተጣሉ ከ20 በላይ ህፃናትን ሰበሰብኩ። ህይወቴም በቀድሞው መልኩ ሊቀጥል አልቻለም። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ህፃናትን፣ ቤተሰቦቻቸውንና ማህበረሰባቸውን እየተንከባከብኩ፣ ፈጣሪ የሚወደውን ሥራ እየሰራሁ እገኛለሁ፤ ብቻዬን አይደለሁም፤ እግዜአብሄር በርካታ ሥራዬን የሚያግዙና የሚደግፉ ቀና ሰዎችን ይልክልኛል። አሁን ደግሞ ይህ የጀመርኩት ሥራ በኢትዮጵያ ሕዝብ ባለቤትነት እየተመራ እንዲቀጥል እፈልጋለሁ።

በሰሜን ሸዋ ሸበል በተባለች አነስተኛ መንደር የተወለድኩት ከጣልያን ወረራ አንድ ዓመት በኋላ፣ በ1929 ዓ.ም ሳይሆን አይቀርም። የጣልያን ወራሪ ኃይልን ለመከላከል የዘመቱት አርበኛ አባቴ፤ ውጊያ ላይ የሞቱት ጨቅላ ህጻን ሳለሁ ነው:: ከአባቴ ህልፈት በኋላ፣ እናቴ ወደ ቤተሰባቸው ስለሄዱ የአባቴ ወገኖች፣ አያቶቼ ናቸው ያሳደጉኝ። ዘጠኝ ዓመት ሲሞላኝ፣ እናቴ የእሳዳጊነት ሙግት አሸንፈው ቢወስዱኝም ከሦስት ዓመት በላይ አልቆየሁም። 12 ወይም 13 ዓመት ገደማ ሲሆነኝ፣ እናቴ ሊድሩኝ በመፈለጋቸው ከቤት ጠፍቼ ኮበለልኩ። በዚያ ለጋ እድሜ ከቤት ወጥታ ለማታውቅ ሴት፤ ኩብለላ ምን ያህል አስፈሪ እንደነበር አስቡት። ወዴት እንደምሄድ አላውቅም ነበር። ሰው እንዳያየኝና ይዞ እንዳይመልሰኝ፣ ቀን ቀን ዛፍ ላይ እየተኛሁ፣ ማታ ስጓዝ አድራለሁ። በመጨረሻ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ የጭነት መኪና የማገኝበት ቦታ ደረስኩና፣ አጎቴ የሰጠኝን ስድስት ብር ከፍዬ ተሳፈርኩ።

አዲስ አበባ ከደረስኩ በኋላም የማውቀውም ሆነ የምሄድበት ቦታ አልነበረኝም። እንደ እድል ሆኖ ፒያሳ የጉምሩክ ባለሥልጣን መሥሪያቤት በር አጠገብ ደከሞኝ የመብራት ምሰሶ ተደግፌ አረፍ አልኩ። የሥራ መውጫ ሰዓት ስለነበር፣ የመሥሪያቤቱ አስተዳደር ከቢሮዋቸው ሲወጡ አዩኝና ጠጋ ብለው ስለ አመጣጤ ሲሰሙ አዝነውልኝ እዚያው አካባቢ ወዳለ መኖርያ ቤታቸው ወሰዱኝ። ባለቤታቸው ታሪኬን ሲሰሙ አለቀሱ። ለካስ እሳቸውም እንደኔ ከቤታቸው ኮብልለው የጠፉ እህት ነበራቸው። እምጥ ትግባ ስምጥ አልታወቀም። ባልና ሚስቱ የቤተሰባቸው አባል አደረጉኝና እንደ ልጃቸው አሳደጉኝ። አያቴ “ትምህርት ሃይማኖትን ያስለውጣል" ብሎ የነገረኝን ስላልረሳሁ ትምህርት ቤት ሊያስገቡኝ ሲሉ አሻፈረኝ አልኳቸው። ትምህርቱ ቀርቶ ቤት ውስጥ የእጅ ሥራ ጀመርኩ። በኋላም በተለያዩ ፋብሪካዎች ውስጥ እያስቀጠሩኝ ሠራሁ። ሥራ ላይ ጎበዝ ስለነበርኩ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በቡና ማቀነባበርያ ፋብሪካ ውስጥ የጥራት ተቆጣጣሪ ሆንኩ። ከዚያም ትዳር መሠረትኩ።

ወደ ግሸን ማርያም ገዳም የሚወስደውን መንገድ ለማሰራት የገንዘብ ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ ውስጥ ገብቼ፣ ገንዘቡ ከተሰበሰበ በኋላ ወደ ግሸን ለመሄድ ወሰንን። እግረ መንገዳችንን ሃይቅ የሚገኘውን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ጎብኝተን ስናልፍ፣ በየሜዳው ቁጥር ስፍር የሌለው ሕዝብ ተጋድሞ አየንና ጠጋ ብለን ተመለከትን። መንግሥት ለመደበቅ የሚሞክረው እጅግ የከፋ ረሃብ ተጎጂዎች መሆናቸውን ተገነዘብን። ከቦርሳዬ ውስጥ ዳቦ አውጥቼ ለሁለት ልጆች ልሰጣቸው ስሞክር፣ ፖሊሶች ደርሰው "ከዚህ አካባቢ ጥፊ" አሉኝ። "እሞታታለሁ እንጂ ንቅንቅ አልልም" አልኳቸው። እዚያው አጠገቤ ደግሞ አንዲት ጨቅላ፣ መሬቱ ላይ የተጋደመችውን ሴት ጡት ጎርሳ ትጠባለች። እናቲቱ ህይወቷ አልፎ ስለነበር አትንቀሳቀስም። ወዲያው ሁለመናዬ ተናወጠ። እንደዚያ ዓይነት ሰቆቃ በህይወቴ ሙሉ አይቼ አላውቅም። ፖሊሶቹ በድጋሚ



ወ/ሮ አበበች በልጅነታቸዉ



ወ/ሮ አበበች ከሥራ ባልደረባቸው ጋር የድርጅታቸው ጊቢ ውስጥ

## “ከሁሉም በላይ ትልቅ ደስታ የሚሰጠኝ የማሳድጋቸው ልጆች ለወግ ለማዕረግ በቅተውና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች ሆነው ማየት ነው።”

ዞር በይ ሲሉኝ፣ ህፃኗን እንዲሰጡኝ ለመንኳቸው። መጀመርያ ላይ ሊገድሉኝ ሁሉ ዝተውብኝ ነበር። እንባና ልመና ሲሰለቻቸው ግን ፈቀዱልኝ። ጨቅላዋን በነጠላዬ ጠቅልዬ በረርኩ። በማግስቱ ወደ ግሸን ስናመራ የገጠመን ደግሞ የባሰ ነበር። በግራና በቀኝ በሺ የሚቆጠሩ የረሃብ ተጎጂዎች የሞት አፋፍ ላይ ሆነው ሲሰቃዩ ነበር። ያደርንባት መንደር አንድ ዛፍ ስር፣ የአንድ ቤተሰብ አባላት ኩርምት ብለው አገኘን። ሦስቱ በህይወቱ የሉም። አባትየውና የታቀፋት ህፃንም ደክመዋል። ትንሽ ቆይቶ አባትየው ልጁን እንድናሳድግለት እየተማፀነን ህይወቱ አለፈ። ከመቅዐበት ህፃኗን አንስቼ አቀፍኳት። በሁለት ቀናት ከሟች ወላጆቻቸው እቅፍ የወሰድኳቸውን ሁለት ህፃናት ይዤ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ግን የድሮዋን አበበች አልነበርኩም፤ ተለውጫለሁ። ሥራዬና ትዳሬ እንደበፊቱ ገዝፈው አልታይሽ አሉኝ፣ ትርጉም አጣሁባቸው። ያኔ በረሃብ የተጎዱ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ መጉረፍ የጀመሩበት ወቅት ሲሆን እኔም ከ20 በላይ ህፃናትን ከየጎዳናው በመሰብሰብ ከባለቤቴ ጋር ተጋጨን። እናቴ ሳትቀር ሁሉም ሰው ድርጊቴን ተቃወሙኝ። ኑሮዬ ተመሰቃቀለ። አንድ ቀን ሲጨንቀኝ ህፃናቱን ሰብስቤ አቅራቢያችን ጫካ ውስጥ ወደነበረው የዶሮ ማርቢያዬ ሄድኩና አዚያ መኖር ጀመርን። ጅቦች የሚተራመሱበት ቦታ ስለነበር፣ ህፃናቱን እንዳይተናኮሉብኝ ፈርቼ ነበር። ደግነቱ ግን አልደረሱብንም። እንደውም ከክፉ ነገር የሚከላከሉን ነበር የሚመስሉት።

ስለእኛ ወሬው በየቦታው ሲዳረስ በርካታ ችግረኛ እናቶች፣ ህፃናት ልጆቻቸውን ፖሊስም ወላጆቻቸው የጣሏቸውን ህፃናት እንዳሳድግላቸው ያመጡልኝ ጀመር። የማሳድጋቸው ህፃናት ቁጥር አርባ ደረሰ። ቀስ በቀስ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድርጅቶች እርዳታ ይሰጡን ጀመር። መጀመርያ ላይ የካቶሊክ ተራድኦ አገልግሎት እና የጀርመኑ “ሜንሽን ፎር ሜንሽን” ለህፃናቱ ምግብ በማቅረብ አገዙን። የክርስትያን በጎ አድራጎት ድርጅት ደግሞ ስንዴ አቀረበልን። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የህፃናትና ትምህርት ደጓሚ፣ አንድ የልብስ ስፌት ማሽን ሰጠን፤ ሁለት ክፍሎችንም ሰራልን። መንግሥት ሰፊ ግቢ ከሰጠን በኋላ፣ አሁን የምንጠቀምባቸውን መኝታ ቤቶች፣ የሥልጠና ማዕከላት፣ ትምህርት ቤትና ሆስፒታል ለመገንባት ከበርካታ ምንጮች ድጋፍ አገኘን። ለዓመታት ከጎኔ ሳይለዩ በዚህ የፈጣሪ ሥራ ሳበረታቱኝና ድጋፋቸውን ለሰጡኝ ሁሉ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። የህፃናት ማሳደጊያ ለማቋቋም በተለያዩ ቦታዎች መሬት የሰጠኝንም መንግሥት አመሰግነዋለሁ። በአምቦ አቅራቢያ በጉደር እርሻ፣ በአዲስ አበባና በቡራዩ ት/ቤቶች እንዲሁም ሆስፒታሎችንና ሌሎች ማሳደጊያውን የሚደግፉ የንግድ ድርጅቶችን የጀመርነው መንግሥት በሰጠን መሬት ላይ ነው።





ህፃናት ማሳደጊያውን ስጀምር በምን መንገድ ድጋፍ እንደማገኝ የማውቀው ነገር አልነበረም። በተለያዩ ሥራዎች ገንዘብ ለማግኘት መጣጣሬ ግን ልቀረም። በ1983 ዓ.ም ገደማ ድርጅታችን ህጋዊ ምዝገባ ባገኘ በአራተኛው መቱ፣ በእርሻ ሥራ የህፃናቱን ምግብ ለማሟላትና ትርፍ ምርቶችን በመሸጥ ገቢ ምንጭ ለማግኘት ከመንግሥት መሬት ጠየቅሁ። እምቦ አቅራቢያ መሬት ተሰጠን ወዲህ በአካባቢው ገበሬዎች ድጋፍ ጤፍን ጨምሮ በርካታ የእህል ዓይነቶች በማምረትና እንስሳት በማርባት፣ የራሳችንን ምግብ ለማሟላትና ገቢ ምንጭ ለመፍጠር ችለናል። በእኔ አስተሳሰብ ገንዘብ ከመለመን ይሄ ተሻለ ዘዴ ይመስለኛል። ከዚህ በተጨማሪ እንጀራ፣ ጠጅ፣ በርበሬና ሌሎች ባልትና ምርቶችን እያዘጋጀን ለትላልቅ ሆቴሎች እንሸጣለን። ከገቢ ምንጭነቱ ሻገር ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል የሚከፍት ሲሆን ህፃናቱንም ከሥራ ጋር ንዲተዋወቁ ያደርጋል።

ሬ ድርጅታችን የህፃናቱን ማሳደጊያ ከማስተዳደርም በተጨማሪ፣ ህፃናትንና ሳጅ ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ በርካታ ሥራዎችን ያከናውናል። በአዲስ በባና በኦሮምያ ክልል በብዙ ቦታዎች ላይ እንሰራለን። በድህነት የሚማቅቁ ማህበረሰቦችን ለማገዝና እናቶች የኢኮኖሚ አቅማቸውን አጎልብተው ጆቻቸውን ማሳደግ እንዲችሉ፣ በርካታ ተቋማትን ገንብተናል። እናቶች ልጆቻቸው ጤናማ ይሆኑላቸው ዘንድ በሴቶች ጤናና በቤተሰብ ምጣኔ ድጋፍ ንሰጣለን።

ህፃናትን ወደ ማሳደጊያ ተቋሙ አምጥተን የምናሳድገው ሌላ አማራጭ ካጣን ብቻ ነው። ቅድምያ የምንሰጠው ህፃናቱ ከዘመዶቻቸው ወይም በማደጎና በጉዲፈቻ ከሚያሳድጓቸው ጋር በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖሩ ነው። ለታዳጊዎች ትምህርትና ሥልጠና የምንሰጠው ራሳቸውን ችለው ህይወታቸውን ከመምራትም ባሻገር፣ ለማህበረሰቡ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ዜጎች እንዲሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ትልቅ ደስታ የሚሰጠኝ የማሳድጋቸው ልጆች፣ ለወግ ለማዕረግ በቅተውና ኃላፊነት የሚሰማቸው ሰዎች ሆነው ማየት ነው። ብዙዎቹ በዲግሪና በዲፕሎማ ተመርቀዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ብርቅና ድንቅ የሚባል ስኬት ላይ ደርሰዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ይህን ድርጅት እንደራሱ ቆጥሮት፣ በባለቤትነት ስሜት ሥራውን ወደፊት እንደሚገፋበት ተስፋ አደርጋለሁ። ይኄ ሥራ እስከተፈለገበት ጊዜ ድረስ እንደ ቀይ መስቀል በመላ አገሪቱ ተስፋፍቶ ለማየት እመኛለሁ። ይህንንም ለማሳካት በሞት ከተለዩን ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር እንዳደረግሁት ሁሉ፣ ወደፊትም ከኢትዮጵያ መንግሥታት ኃላፊዎች ጋር በቅርበት መሥራቴን እንደምቀጥልበት ተስፋ አለኝ። አምስት የልብ ቀዶ ህክምናን ጨምሮ ከ17 በላይ ቀዶ ህክምናዎችን አድርጌ በሕይወት የተረፍኩት እግዚአብሔር ይሄን ሥራ እንድሰራ በመፈለጉ እንደሆነ አምናለሁ።


ሴቶች ከወንዶች እኩል እድል ከማያገኙበት የድሮው ዘመን ጋር ሲነፃፀር፣ የዛሬዎቹ ወጣት ሴቶች ህይወታቸውን በመረጡት መንገድ የመምራት መብት አግኝተዋል ማለት ይቻላል። ሴቶች በበታችነት የወንዶች አገልጋይ ሲሆኑ ማየት አልወድም። ይህን ስል ግን ሴቶች ያልተገባ የበላይነት ይኑራቸው ማለቴም አይደለም። ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች የዛሬውን የተሻሻለ ዘመን ተጠቅመው፣ ትጋት በመሥራት እምቅ አቅማቸውን እንዲያሳዩ እፈልጋለሁ። ከጥገኝነት ላቀውና ራሳቸውን ችለው፣ በራሳቸው ውሳኔ ኑሯቸውን መምራትና ኃላፊነት ስሜት ልጆቻቸውን ማሳደግ ይኖርባቸዋል። የተቸገሩ ሰዎችንም መርዳት ይገባቸዋል። በዚህ መንገድ አገራቸውን ሊያግዙ ይችላሉና። እኛ ሴቶች በቅጡ ከሰራን፣ የወንድ አውራ ከሚባለው ሠራተኛ ባልተናነሰ ጥራትና ፍጥነት ሥራችንን የማናከናውንበት ምክንያት የለም።



ወ/ሮ አበበች በቢሮአቸዉ ዉስጥ ከሥራ ባልደረባቸዉ ጋር



የ 15 ቀናት እድሜ ያለዉ ህፃን በህፃናት ማሳደጊያዉ ዉስጥ



ልጆች በአበበች ጎበና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ